የኢትዮጵያን ድንበር ለሱዳን እንዳይሰጥ እንዲሁም ኢትዮጵያዉያንን እርስበ በእርስ ከመተላለቅ ለመታደግ ተቃዋሚዎች የጋራ ግብረ ሀይል ይመስርቱ !

================= ሸንቁጥ

አየለ

-ወያኔ ኢትዮጵያን ሳታጠፋ እንቅል አልወስድ ብሏታል። የኢትዮጵያን ድንበር እየሸነሸነች ታድላለች። ኢትዮጵያን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በአራት መልክ አፈርሰዋለሁ ብላ ታጥቃ ተነስታለች:-

1. ህዝቡን በጎሳ በመከፋፈል እርስ በእርሱ እንዲጨራረስ ማድረግ

2. ሀገሪቱን ማስገንጠል

3. የሀገሪቱን ድንበር እየቆረሱ መስጠት

4. ኢትዮጵያዉያን ኢትዮጵያዊነትን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲጠሉት የጸረ -ኢትዮጵያዊነት ስነልቦናን አጥብቆ ማስረጽ

ወያኔ እሩብ ምዕተ አመታት ገዛች። መግዛቱንማ ማን በከለከላት ነበር? ያባቶቿን ሀገር በክብር ቢያንስ አንባገነን ሆና ህዝቡን አክብራ : ኢትዮጵያዊነትን ወዳ መግዛትና ማስተዳደር ብትችል ምን ነበረበት? ዲሞክራት ባትሆንም ኢትዮጵያዊ አንባገነን ሆና ሀገሩን ብታስተዳድረዉ መልካም ነበር።

ወያኔ ግን ከዚህ የከፋዉን መንገድ መርጣለች። እንግዲህ ኢትዮጵያን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማፍረስ ዝግጅቷን አጠናቃ ስትጨርስ የጎንደር ጀግና ህዝብ እንቅፋት ሲሆንባት ጎንደርን መከፋፈል: የጎንደርን መሬት ለሱዳን ቆርሶ መስጠት: ጀግናዉን የጎንደር ህዝብ እርስ በእርሱ ማጋጨት እና የዘር ማጥፋት በኢትዮጵያዉያን መካከል ይከናወነ ዘንድ ሁሉንም ነገር አመቻችታለች። አሁን ጎንደርን ፈጽሞ ለማጥፋት እየተፋጠነች ነዉ።

ህዝቡ አማራና ቅማንት በሚል ወያኔ በሰራችዉ የተንኮል ወጥመድ ዉስጥ ገብቶ እርስ በእርሱ እየተጨራረሰ ነዉ። ወያኔ ከኋላ ሆና ትስቃለች።ይሄ ሁኔታ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ሪፖርት መደረግ አለበት።የተባበሩት መንግስታታ ይሄን ሁኔታ በሚገባ እንዲገነዘበዉ ተቃዋሚዎች የሚያቋቁሙት ግብረ ሃይል ትልቅ ሃላፊነት አለበት።

ስለዚህ ተቃዋሚዎች ባስቸኳይ በሚከተለዉ ጉዳይ ላይ ብቻ ስምምነት በመድረስ አንድ ግብረ ሀይ መመስረት አለባቸዉ። እንድሚታወቀዉ በኢትዮጵያዉያን ተቃዋሚዎች መካከል በርካታ ልዩነቶች አሉ። ቢሆንም በኢትዮጵያዊነት የሚስማሙት ተቃዋሚዎች ሁሉ በጋራ ተሰባስበዉ የኢትዮጵያን ድንበር ለሱዳን እንዳይሰጥ እንዲሁም አሁን ኢትዮጵያዉያን ብሄሮችን እርስበ በእርስ ከመተላለቅ ለመታደግ የጋራ ግብረ ሀይል መመስረት አለባቸዉ።ተቃዋሚዎች ይሄኛዉ የብሄር ድርጅት ነዉ: ይሄኛዉ ህብረ ብሄራዊ ነዉ የሚለዉን አካሄድ መተዉና በኢትዮጵያዊነት የሚያስማማቸዉ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩረዉ መስራት ወሳኝ ግዴታቸዉ ነዉ።

የግብረ ሀይሉ አላማም የሚከተለዉ ይሆናል:-

1ኛ. አሁን ወያኔ ከጎንደር ቆርሳ ለሱዳን የምትሰጠዉን ሀገር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገንዝቦ ወያኔ ላይ ተቃዉሞዉን እንዲያሰማ ለማስቻል

2ኛ. በአካባቢዉ ያሉ ኢትዮጵያዉያኖች ሱዳኖች መሬቱን ልቀቁ ብለዉ ጥቃት ሲሰነዝሩባቸዉ እራሳቸዉን ኢንዲከላከሉ ለማብቃት በብዙ ዘርፍ ማህበረሰቡን ዝግጁ እንዲሆን ማስቻል

3ኛ. አሁን በኢትዮጵያዉያን መካከል የተፈጠረዉ የብሄር ጥላቻ ወያኔ የራሷን አላማ ለማራመድ ጸንሳ የወለደችዉ እንጅ የኢትዮጵያዉያን ማህበረሰቦች ፍላጎት እንዳልሆነ በማስረዳት ኢትዮጵያዉያን ሁሉ እርስ በእርስ ከመጠፋፋት ይልቅ የጋራ ትግላቸዉን አቀናጅተዉ ወያኔ ላይ እንዲያተኩሩ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት

4ኛ/ በኢትዮጵያዉያን መካከል እየተከናወነ ያለዉ የእርስ በእርስ መጠፋፋት ወያኔ በተንኮል የዘረጋችዉ ፕሮግራም መሆኑን የአለም አቀፍ ማህበረሰብ ተገንዝቦ ወያኔ መንበሯን እንድትለቅ ጫን የሚያሳርፍበትን መንገድ ማጥናትና መቀየስ። ኢትዮጵያ እንደ ሩዋንዳ አይነት ሁኔታ ዉስጥ ሳትገባ ሁኔታዎች በእንጭጩ የሚቀጩት ወያኔ ከመንበሩ ስትለቅ መሆኑን አለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲገነዘበዉ ማድረግ

5ኛ/ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዉያን ከፈጽሞ ጥፋት ለመታደግ የሚያስችል አቻቻይ የፖለቲካ ፕሮግራሞችን ሁሉንም ማህበረሰብ በማካተት ለመንደፍ ጥናት እንዲያደርግ

ተቃዋሚዎች እንግዲህ ወያኔ እንዲህ አደረገችን : ይሄን በደለችን እያሉ ማላዘናቸዉን መተዉና በጋራ መሰባሰብ የጋራ ግብ መንደፍ በሚያስማማቸዉ ትልቅ ጉዳይ ላይ ብቻ በጋራ መስራት አለባቸዉ። ተቃዋሚዎች ይሄኛዉ የብሄር ድርጅት ነዉ: ይሄኛዉ ህብረ ብሄራዊ ነዉ የሚለዉን አካሄድ መተዉና በኢትዮጵያዊነት የሚያስማማቸዉ ጉዳይ ላይ መስራት ወሳኝ ግዴታቸዉ ነዉ።

አገሩ ፈጽሞ እርስ በእርስ ጦርነት ዉስጥ ከገባ ብኋላ መራወጡ አንድም የሚያተርፈዉ ነገር እንደሌለ ተገንዝቦ ሁሉም ከተኮፈሰበት ወንበር ላይ እየወረድ አንዱ ወዳንዱ ይቅረብ። አንዱም አንዱን ያነጋግር። አንዱም አንዱ አማላጅ ልኮ እስኪያነጋግረዉ አይጠብቅ።

ኢትዮጵያ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ ከፈጽሞ መጥፋት ትድናለች !